# የጨረታ ማስታወቂያ
## ብ/ግ/ጨ/10/2015

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2015 በጀት ዓመት ለጤና ሣይንስ ኮሌጅ የላብራቶሪ ዕቃዎችን በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም ዕቃውን ማቅረብ የምትፈልጉ ተጫራቾች፡-

1. በዘመኑ የታደሰ ንግድ ሥራ ፈቃድ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የቲን ምዝገባ የምስክር ወረቀት ከሚመለከተው የመንግስት አካል ማቅረብ የሚችሉ፣
   - ተጫራቾች የጨረታ ሰነዳቸውን ዋጋ ሞልተው ሲመልሱ የጨረታ ማስከበሪያ ብር 200,000.00/ሁለት መቶ ሽህ/ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ የባንክ ዋስትና በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስም አሠርተው ማቅረብ ሲኖርባቸው በጥቃቅን የተደራጁ ከአደራጃቸው የመንግስት መ/ቤት የዋስትና ደብዳቤ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስም በማሠራት ማቅረብ አለባቸው፣
2. አሸናፊው ተጫራች አሸናፊነቱ በተገለፀለት ከ7/ሰባት/ ተከታታይ የሥራ ቀናት በኋላ በግንባር ቀርቦ አሸናፊ የሆነበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% የውል ማስከበሪያ በማስያዝ በ8 ቀናት ውስጥ ውል መያዝ የሚችል መሆን አለበት፣
3. ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች የጨረታ ዶክመንቱን ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 እና አዲስ አበባ አራት ኪሎ ከቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ወረድ ብሎ ሮሚና ካፌ ህንፃ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 07 ድረስ በመቅረብ ማስታወቂያው <u>በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ</u> <u>ለተከታታይ 30 ቀናት</u> የማይመለስ ብር 200.00/ሁለት መቶ/ በመክፈል ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፣
4. ተወዳዳሪ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን በአግባቡ በመሙላትና በማሸግ <u>በ31ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡59 ድረስ</u> ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ድረስ በመቅረብ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፣
5. ጨረታው <u>በ31ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00</u> ተዘግቶ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት <u>በዚሁ ቀን ከጠዋቱ 4፡30</u> በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 27 በግዥ ቡድን ቢሮ ቁጥር 10 ይከፈታል፡፡ ሆኖም ተጫራቾች በጨረታው ላይ መገኘት ካልቻሉ መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ በጨረታው ላይ ያልተገኙ ተጫራቾች ፖስታን ጨምሮ ጨረታው በእለቱ ይከፈታል፡፡
6. የጨረታውን ቴክኒካል እና ፋይናንሽያል ኦርጅናል እና ኮፒ ዶክመንቶች እንዲሁም የጨረታ ማስከበሪያውን ለየብቻ አስተማማኝ በሆነ ማጣበቂያ በታሸገ ፖስታ በማድረግና በእያንዳንዱ ፖስታ ላይ የመ/ቤቱን ሙሉ ስምና አድራሻ በመፃፍ ማህተም በማድረግ በተጠቃለለ አንድ ፖስታ በማሸግ ማቅረብ አለባቸው፡፡
7. ዩኒቨርሲቲው ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

<u>ማሣሰቢያ</u>፡- የጨረታ መዝጊያና መክፈቻ ቀኑ ቅዳሜና እሁድ ወይም በበዓል ቀናት ከሆነ ጨረታው በቀጣዩ የሥራ ቀን ተዘግቶ የሚከፈት ይሆናል፡፡

ለበለጠ መረጃ፡- በስልክ ቁጥር 058-771-66-91 ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ**

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የግዥ ሂደት ቁጥር 1
Debre Markos University Procurement Administration Process No 1